FEED THE FUTURE

The U.S. Government's Global Hunger & Food Security Initiative

# የቤተሰብ አባላት መሰረታዊ ለውጥ ስነዘዴ

## የሥልጠና መርጃ



USAID

ከአሜሪካን ሕዝብ



# የቤተሰብ አባላት መሰረታዊ ለውጥ ስነዘዴ

**ተልእኮ:-** ዕየቤተሰብ መሰረታዊ ለውጥ ዋና ተልእኮ በቤተሰብ አባላት መካከል ያለውን ሥርዓተ - ፆታ መስተጋብር በተለይም የጋራ ሃብትን ማግኘት፣ መቆጣጠር እና የስራ ክፍፍል ማድረግ በቤተሰብ አባላተ መካከል ያለውን ሥርዓተ - ፆታ መስተጋብርን በመሰረታዊነት ለመለወጥ ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው።

**የሥልጠናው ዓላማ:-** ይህ ሥልጠና፥ መላው የቤተሰብ አባላት በመካከላቸው ውስጥ ማለትም በወንዶችና በሴቶች፣ እንዲሁም በወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች መካከል ስላለው ሥርዓተ - ፆታዊ መስተጋብር እንዲረዱ የተዘጋጀ ተግባር - ተኮርና አሳታፊ ልምምድ ነው። በሥልጠናው ማብቂያ ላይ ተሳታፊ የቤተሰብ አባላቱ፦

- በቤተሰብ ደረጃ ስላለው ሥርዓተ-ፆታዊ መስተጋብር ይረዳሉ
- በቤተሰቡ ውስጥ ማን ምን እንደሚሰራ እና እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ያለበት የስራ ጫና ምን ያህል እንደሆነ መለየት ይችላሉ
- የትኛው የቤተሰብ አባል የትኛውን ሃብት እንደሚያገኝና እንደሚቆጣጠር እንዲሁም ከተለያዩ የሃብት ምንጮች እንደሚጠቀም ለይተው ያውቃሉ

- የቤተሰብ አባላት ደህንነት፣ ጤንነት፣ ትምህርት እና የሰመረ የእርስበርስ ግንኙነት ስላላቸው አስፈላጊነት ያውቃሉ
- የቤተሰቡ አባላት ያለባቸውን ክፍተት ለማጥበብ/ለመሙላት የሚረዳ የድርጊት መርሃ-ግብር ያዘጋጃሉ

**የሚያስፈልገው ጊዜ:-** 1 - 2 ሰዓት (እንደ ቤተሰቡ አባላት አረዳድ እና የማቻቸት ክህሎት ይወሰናል)

**ተጼራሽ ክፍሎች:-** ሁሉም የቤተሰብ አባላት

**የሥልጠናው ቋንቋ:-** የአካባቢው ማኅበረሰብ ቋንቋ

**የሥልጠናው ቦታ:-** ሥልጠናው አመቻቾቹ እና የአካባቢው ሃላፊዎች ተመካክረው የሚወስኑትና በማኅበረሰቡ አቅራቢያ ቦታ ላይ ይሰጣል

**የሥልጠና መርጃ መሣሪያዎች:-** በአካባቢው የሚገኙ እንደ ጠጠር/ባቄላ፣ ዘር፣ዱላ ወይም ገመድ፣ የሚገኝ ከሆነ ባለቀለም ወረቀቶች ካልሆነም ነጭ ወረቀትና ማርከር/ብዕር የመሳሰሉት

## የማመቻቸት ሂደቶች

የቤተሰብ ሥርዓተ-ምግባር መሰረታዊ ለውጥ ስልጠና የሚከተሉትን ሂደቶች ይከተላል ፡

## ደረጃ 1

- እንደ 1) የቤተሰብ ተጠሪ 2) አባት/እናት 3) ወንድ ልጅ እና 4) ሴት ልጅ ሆነው የሚተውኑ አራት ፈቃደኞችን መምረጥ
- በጎ ፈቃደኞቹ ከመላው ተሳታፊ ፊት ለፊት በመደዳ እንዲቀመጡ ንገሩአቸው
- ብዙሃን ተሳታፊዎቹ መቀመጥ ያለባቸው በግማሽ ክብ ቅርፅ ነው (ስልጠናው በመሃሉ እንዳይቆራረጥ በቤት ውስጥ ወይም በሆነ መጠለያ ስር ቢካሀሄድ መልካም ነው)።


5



# ደረጃ 2

- ለዚህ ተግባር ቀዳሚ ሃላፊነቱን ማን መውሰድ እንዳለበት ከተሳታፊዎቹ ጋር ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ለተሳታፊዎች ሰንጠረዥ እንዴት መስራት እንደሚቻልና እንደሸክም አቅማቸው ድንጋዮችን/ባቄላዎችን እንዴት መደርደር እንደሚቻል ማሳየት

7



## ደረጃ 3

- ዱላዎችን በመጠቀም ሰንጠረዥ መሳልና ተሳታፊዎች እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ ተግባራቱን መፃፍ:: በቤት ውስጥ ስራዎች በመጀመር ለምሳሌ፥ ምግብ በማብሰል፣ ውሃ በመቅዳት፣ የማገዶ እንጨት በመሰብሰብ፣ ልጆችን በመንከባከብ፣ በመጀመር በምርታማ ተግባራት ለምሳሌ እንስሳ ርቢ፣ ወተት ማለብ፣ ማረስ፣ ማረም ፣ ወዘተ በመቀጠል መዘርዘር

- ለመልመጃው ጅማሮ የቤተሰቡ አባላት እንዳላቸው የሃላፊነት ድርሻ (እናት፣ አባት፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ) የትኛው ስራ የየትኛው የቤተሰብ አባል ሃላፊነት እንደሆነ እንዲዘረዝሩና ተሳታፊዎቹን ከ1-10 ያሉትን ቁጥሮች ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በመስጠት እንዲስማሙ ማድረግ:: ከቤተሰቡ አባላት ውስጥ ብዙ የስራ ድርሻ ያለው አባል ዝቅተኛ ወይም ምንም የስራ ድርሻ ካለው አንፃር ከፍተኛ ቁጥር ይሰጠዋል::

- በእያንዳንዱ የ“ቤተሰብ አባል” ፊት ለፊት የተመደበለትን የሃላፊነት ብዛት የሚወክሉ ጠጠሮች ማስቀመጥ

9

- ለዋናዋናዎቹ ስራዎች ትኩረት በመስጠት ሁሉንም የስራ ድርሻዎች ዘርዝሩ። ጊዜ እንዲበቃ የስራ ድርሻዎቹ ብዛት ከ15-20 መብለጥ የለበትም። ይህንን ሂደት ለእያንዳንዱ የመልመጃ ተግባር መከተል።



## ደረጃ 4

- ቤተሰቡ ባጠቃላይ ያለውን ሃብት እንዲዘረዝሩና ከእነዚህ ሃብቶች ውስጥ የትኛው የቤተሰብ አባል የትኛው ሃብት ላይ እንደሚያዝዝ እንዲገልፁ ይጠየቋቸው:: ይህ መልመጃ በዋናነት  የትኛው የቤተሰቡ አባል በተለይ ከትላልቆቹ ወንዶችና ሴቶች መሃል ማንኛቸው በቤተሰቡ ንብረትና ሃብት ላይ የአጠቃቀምና የቁጥጥር ሥልጣን እንዳለው መመልከት ላይ ያተኩራል:: አብዛኛዎቹ የቤተሰቡ አባላት በተወሰኑት የቤተሰቡ ንብረቶች ላይ የማዘዝ ሥልጣን ሊኖራቸው እንደሚችል  ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፥ አባላቱ የሚስማሙበትን የጠጠር ብዛት በእያንዳንዱ የመድረክ ተሳታፊ ፊት መደርደር::

- በቤተሰቡ ውስጥ ያሉት የስራ ድርሻዎችና ንብረቶች/ሃብቶች በሙሉ ከተዘረዘሩ በኋላ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የየራሱን ጠጠሮች እንዲቆጥር ያድርጉ::




## ደረጃ 5

- **እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ያገኘውን የጠጠር ብዛት ጠቅላላ ውጤት ለመላው ተሳታፊዎች በማሳወቅ ለምን የተወሰኑት የቤተሰቡ አባላት ከሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት የበለጠ የጠጠር ብዛት ሊኖራቸው እንደቻለ በመጠየቅ ተወያዩበት።**

- **አመቻቹ፥ ተሳታፊዎች በተቻለ መጠን ከውጤቱ በስተጀርባ ያሉትን ምክንያቶች እንዲመረምሩ ለማበረታታት የምክንያት እና ውጤት ትንተና ዘዴን እንዲጠቀሙ ይመከራል። አመቻቹ ሊጠቀሟቸው ከሚችሏቸው ጥያቄዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፦**

  - ስለመልመጃው ምን ተሰማቻሁ?
  - ምን ተማራችሁ?
  - ለምንድን ነው የተወሰኑትን ስራዎች ሴቶች ብቻ የሚሰሯቸው? እነዚህን ስራዎች ወንዶቹ ለምን አይሰሯቸውም፤ ሴቶቹስ የወንዶቹን እንደዚሁ ለምንድን ነው የማይሰሩት?
  - በቤተሰቡ ገቢ/ጤና/ትምህርት/የስራ ጫና ላይ ያለው ተፅእኖ ምን ይመስላል?
  - ማን ነው በቤተሰቡ ሃብት እና ጥቅም ላይ ይበልጥ የማዘዝ ሥልጣን ያለው? ለምን?
  - ይህ በቤተሰቡ አባላት መካከል ያለው የሰመረ ግንኙነት ላይ፣ ምርታማነት ላይ፣ ተጠያቂነት/ሃላፊነት ላይ፣ ኢኮኖሚ ላይ፣ ወዘተ ያሉት ተፅእኖዎች ምንድን ናቸው?



# ደረጃ 6

በመቀጠል አመቻቹ የሚከተለውን ጥያቄ ማቅረብ አለበት፦ እነዚህን ግኝቶች በሚመለከት ምን መደረግ አለበት? የቤተሰብ አበላት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለማቅረብ ግንባር ቀደም መሆን አለባቸው። የሚከተሉት ትኩረት ይሻሉ፦

- o የስራዎቹ ይዘትና መጠን ከቤተሰብ ቤተሰብ ይለያያል
- o አመቻቹ የቤተሰብ አባላቱ የድርጊት መርሃ-ግብር በራሳቸው እንዲያመነጩ ማበረታታት እንጂ መምራት የለባቸውም፡፡

- **ተሳታፊዎች ሁኔታውን እንዴት መለወጥ እንደሚችሉ ማሰብ እንዲጀምሩና ለቤተሰባቸው የተግባር እቅዱን እንዲያጋሩ በመጠየቅ ክፍለጊዜውን ያጠናቅቁ፡፡**

ማስታወሻ:- የሥርዐዓተ-ፆታ ሚናዎች በማህብረሰብ የሚገነቡ ናቸው፡፡ የምንማራቸውም በማህበረሰብ እና በመዋቅሩ ውስጥ ስንኖር ራሳችንን ከፆታችን(ወንዶች፣ ሴቶች፣ ጎረምሶች፣ ኮረዶች ከመሆናችን) አንፃር በምንወስደው ማህበራዊ ገፅታ ነው፡፡ ይህም በቤተሰብ፣በማህበረሰቡ እና በተቋማት ውስጥ በሚኖረን ሚና እና ሃላፊነት፣ በሃብትና ንብረት ላይ በሚኖረን የማግኘት እና የማዘዝ ስልጣን፣ ዕድሎችን በመጠቀም እና ፈታኝ ሁኔታዎችን በመቋቋም ችሎታችን ላይ የራሳቸው የሆነ ተፅእኖ ይኖራቸዋል፡፡



# ምሳሌ:-

የተግባራት ዝርዝር (ምርታዊ እና እርባታዊ) እና ሃብቶች

| ተግባራት | ወንዶች | ሴቶች | ወጣት ወንዶች | ወጣት ሴቶች |
|---|---|---|---|---|
| ምግብ ማብሰል | | XXX | | XX |
| ልብስ ማጠብ | | XXX | X | XX |
| ውሃ መቅዳት | | | | |
| እርሻ ማረስ | | | | |
| ማረም | | | | |
| ምርት መሰብሰብ | | | | |
| ቆሻሻ ማስወገድ | | | | |

| የእንስሳ ሃብት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማርባት | | | | |
| ማለብ | | | | |
| የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበር | | | | |
| **እርሻ-ነክ ያልሆኑ** | | | | |
| አነስተኛ ንግድ | | | | |
| ዳንቴል/ጥልፍ ስራ | | | | |

| ሃብት (የማግኘትና የመቆጣጠር ሥልጣን) | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የከብት ሃብት | | | | |
| መሬት | | | | |
| ቤት | | | | |
| የቤት ውስጥ ዕቃዎች | | | | |
| ገንዘብ | | | | |

Illustration & Designed by Dess Advertising Plc.
0911 38 05 72

FEED THE FUTURE
The U.S. Government's Global Hunger & Food Security Initiative



USAID
ከአሜሪካን ሕዝብ